የመ/ቁ. 190836

ቀን 01/02/2016 ዓ.ም

ለፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የካ ምድብ ችሎት

<u>አዲስ አበባ</u>

ከሳሽ:---- የኢትዮጵያ ማየትና መስማት የተሳናቸው ብሄራዊ ማኅበር

አድራሻ፦ አዲስ አበባ ከተማ አራዳ ክፍለከተማ ወረዳ 6 የቤት ቁጥር 691

ተከሳሽ:------- ጋርዲያን ሴኩሪቲ ኤንድ ጀነራል ሰርቪስ

አድራሻ፦ አዲስ አበባ ከተማ የካ ክፍለከተማ ቀበሌ 16 17 18 የቤ/ቁ 301

<u>በፍ/ብ/ስ/ስ/ሕ/ቁ 276(1) መሰረት የተደረገ የእርቅ ስምምነት ውል</u>

<u>የእርቅ ስምምነቱ መግለጫ</u>

ሀ/ ይህ የእርቅ ስምምነት በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ የካ ምድብ ፍትሀ ብሄር ችሎት እየተደረገ ያለውን ክርክር የሚመለከት ነው::

ለ/ እርቁ ግምቱ 602,200/ስድስት መቶ ሁለት ሺህ ሁለት መቶ/ ብር የሚገመት በጥበቃ ስራ የጠፉ እና የጥገና ወጪ የንብረት ግምት ከነወለዱ ለማስከፈል በሚል ያቀረበውን ክስ እና በመ/ቁ 190836 እየተደረገ ያለውን የፍትሀ ብሄር ክርክር የሚመለከት ነው። ::

ሐ/ ይህ የእርቅ ስምምነት የተደረገው ስማችን እና አድራሻችን ከላይ በከሳሽነትና በተከሳሽነት በተገለጸው ወገኖች መካከል ነው::

<u>የእርቅ ስምምነቱ ፍሬ ነገር</u>

ከሳሽ እና ተከሳሽ ከላይ በተጠቀሰው ፍርድ ቤት እና የመዝገብ ቁጥር እየተደረገ የሚገኘውን በጥበቃ ስራ የጠፉ እና የጥገና ወጪ የንብረት ግምት ከነወለዱ ይከፈለኝ ክስ ጉዳይ በሚከተለው መልኩ በስምምነት ለመፍታት ተስማምተዋል:-

